

# ብፁዕ አቡነ ብርሃነየሱስ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን የ2002 ዓ.ም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ በዓልን በማስመልከት ለምዕመናን ያስተላለፉት መልእክት

**በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡**

**ክቡራን ምዕመናን፣**
**በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የምትገኙ ኢትዮጵያዊያን፣**
**ክቡራን የቤተክርስቲያን አገልጋዮችና፣**
**በጎ ፍቃድ ያላችሁ ወገኖች ሁሉ፣**

**«በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ምክንያት ህያው የሆነውን ተስፋ የሰጠን፣ በታላቅ ምህረቱ በአዲስ ልደት ልጆቹ ያደረገን፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የሆነ አምላክ ይመስገን» (1 ጴጥ 1፣3)፡፡**

ከሁሉ በማስቀደም የዘመናትና የሕይወታችን ባለቤት የሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እንኳን ለ 2002 ዓ.ም. የትንሣኤ በዓል በሰላም አደረሳችሁ በማለት መልካም ምኞቴን በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንና በራሴ ስም እገልጻለሁ፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት ከሞት ተነሥቶአል፡፡ በክርስቶስ ትንሣኤ ሞት መውጊያው ጠፍቶ መሠረቱ ተነቅሎአል (1ቆሮ 15)፡፡ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለም፡፡ በመሆኑም ትንሣኤ የደኅንነታችን ማረጋገጫ የተከናወነበት ታላቅ ምሥጢር ነው፡፡

ትንሣኤና ተስፋ እነዚህ ሁለት ቃላት አንደኛው ከአንደኛው ጋር የሚያያዙ ናቸው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ባይነሣ ኖሮ ተስፋችን የጨለመና ደኅንነታችንም ባልተረጋገጠ ነበር፡፡ ስለሆነም የክርስቶስ ትንሣኤ ለኛ ለክርስቲያኖች የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ተስፋ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ «በክርስቶስ ተስፋ የምናደርገው ለዚህ ዓለም ሕይወት ብቻ ከሆነ ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ የሚታዘንልን መሆናችን ነዋ» ይለናል (1 ቆሮ፣ 15፡19)፡፡

የትንሣኤው ደስታ የዕለት ደስታ ብቻ ሳይሆን፣ የዘለዓለም ደስታ እንዲሆንልን መልካም ሥራን በወንድሞችና በእህቶች መካከል በማድረግ ማስመስከር መቻል አለብን፡፡ በክርስቶስ ትንሣኤ የእርሱ ሰላምና እርቅ ለእኛ ለሰው ልጆች እንዲሆንና እኛም የሰላም ሰዎች ሆነን እንድንገኝ ያስፈልጋል፡፡

እንደሚታወቀው በየዓመቱ የትንሣኤን በዓል እናከብራለን፡፡ ሆኖም በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ምንም ያህል ለውጥ አላሳየን ይሆናል፤ ይህ ለምን ሆነ? ስንል ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላም የኃጢያትን መንገድ ይዘን ስለምንጓዝ ነው፡፡ ሆኖም ሕይወታችንን በጥሩ ነገሮችና ምግባሮች እንድናሳድግና ለክብር በማብቃት እምነታችንን በእውነትና በፍቅር ይዘን እንድንጓዝ ያስፈልጋል፡፡

እኛ በእርሱ ሕይወትና ትንሣኤ ምክንያት አዲስ ፍጥረት ሆነናል፡፡ በሞቱና ትንሣኤው ከእግዚአብሔር እርቅ አግኝተናል፡፡ በሞቱና በትንሣኤው እንፀድቃለን፡፡

የክርስቶስ ትንሣኤ እውነተኛ ነው፡፡ መቃብሩን ፈነቃቅሎ ተነስቷአል (ማር 16፡4)፡፡ አሁን ያለው በአባቱ ቀኝ እጅ ነው (ማር 16፡19)፡፡ በመላዕክት ታጅቦ አንድ ቀን በክብር ይመጣል (ማቴ 25፡31)፡፡ እኛም ክርስቲያኖች ስንሞት በክርስቶስ ትንሣኤ ህያው እንደምንሆን ስለምናምን በእርሱ ላይ እምነታችንን በማጽናት ልንኖር ይገባል፡፡

የተወደዳችሁ ምዕመናን:- በዚህ የተቀደሰ በዓል እንደተለመደው ሁሉ የተቸገሩትን ወገኖች እንድናስብ፣ በአካባቢያችን የታመሙትን በመጠየቅና በመንከባከብ፣ በተለይ በኤችአይቪ በሽታ የታመሙትን፣ አቅመደካሞችን፣ ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያት ላጡ ሕፃናት፣ የጐዳና ተዳዳሪዎች በዓሉን በደስታ ማክበር እንዲችሉ እንደየአቅማችን የምንችለውን በማድረግ እነርሱን ስለ እግዚአብሔር ብለን እንድንረዳቸው አደራ እላለሁ:: «እያንዳንዱ ሰው በቅሬታ ወይም በግዴታ ሳይሆን በልቡ ያሰበውን ያህል ይስጥ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ሰው ይወዳል» (2ቆሮ 9:7):: ይህም የተቸገሩትን መርዳት ባህላችን በታላላቅ በዓላት ጊዜ ብቻ መወሰን እንደሌለበት ለመግለጽ እወዳለሁ::

የአገራችን ዜጐችም ጤናቸውን በመጠበቅ ከሙስና በመጽዳት በልማት ሥራ ላይ የተያዘውን ትልቅ ለውጥ አጠናክረው መቀጠል ያለባቸው መሆኑን እገልጣለሁ:: ፓርቲዎች በጋራ የሥነ ምግባር ደምብ ማጽደቃቸውና በዚሁም ለመመራት መስማማታቸው በአገራችን የተጀመረውን ዲሞክራሲያዊ ሂደት ያጐለብተዋል:: ስለሆነም በመጪው ግንቦት አስራ አምስት ቀን ሁለት ሺህ ሁለት ዓመተ ምህረት የሚካሄደው አራተኛው ብሔራዊ ምርጫ ሰላማዊ፣ ነፃ፣ ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ምዕመናን ሁሉ ጸሎት እንዲያደርጉና በምርጫው በመሳተፍ የዜግነት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ አደራ እላለሁ::

በመጨረሻም ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች፣ በተለይም በየቤቱና በየሆስፒታሉ ላላችሁ ሕመምተኞች፣ ከቤተሰቦቻችሁ በተለያየ ምክንያት ርቃችሁ ለምትገኙ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፣ በእስር ቤት ለምትገኙ ወገኖች ሁሉና ለአገር ደኅንነት በጠረፍና በድንበር ጥበቃ ላይ ለተሰማራችሁ ሁሉ እንኳን ለሁለት ሺ ሁለት ዓመተ ምህረት ለብርሃነ ትንሣኤ በዓል በሰላም አደረሳችሁ በድጋሚ በማለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልባችንን፣ ቤታችንንና፣ አገራችንን ኢትዮጵያን በሰላሙና በብርሃኑ ይጐብኘልን፣ ይጠብቅልን:: አሜን::

**የተባረከ የትንሣኤ በዓል ለሁላችን ይሁንልን::**

**እግዚአብሔር አገራችንን ኢትዮጵያን ይባርክልን::**